# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ
# ADDIS NEGARI GAZETA
## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Twenty Ninth Year No.75
Addis Ababa 04th Day of April, 2024


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፩፻፷፭/፪ሺ፲፮**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ**
**ገፅ............................................... ፫ሺ፫፻፹፮**


**Content**


**Regulation No. 165/2024**
**A REGULATION ISSUED TO REGULATE THE VEHICLE PARKING SERVICE IN ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT**
**Page ............................................... 3386**


## ደንብ ቁጥር ፩፻፷፭/፪ሺ፲፮
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት፣ የትራፊክ ፍሰትን ማስተካከል እና የትራፊክ አደጋን መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀፅ ፺፭ በተሠጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፩፻፷፭/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## Regulation No. 165/2024
## A REGULATION ISSUED TO REGULATE THE VEHICLE PARKING SERVICE IN ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT

**WHEREAS,** it is necessary to establishing a vehicle parking service administration system in Addis Ababa City Administration is necessary to regulate traffic flow and reduce traffic accidents;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 95 the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

### PART ONE
### GENERAL PROVISIOS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "Regulation No. 165/2024 of the Vehicle Parking Service in Addis Ababa City Government''.


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **“ከተማ”** ማለት አዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **“ከተማ አስተዳደር”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **“ቢሮ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

፬. **“ባለሥልጣን”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ነው፤

፭. **“ትራፊክ ተቆጣጣሪ”** ማለት የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና የትራፊክ ሥርዓት በማስከበርና አፈፃፀሙን ለመቆጣጠርም ሆነ የትራፊክ ፍሰትን በማስተናበር በህግ ስልጣን የተሰጠው ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ወይም የባለሥልጣኑ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ነው፤

፮. **“ተሽከርካሪ”** ማለት በከተማው ውስጥ የሚገኝ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የሚጠቀም ማንኛውም ባለሞተር ወይም ሞተር አልባ ተሽከርካሪ ነው፤

፯. **“ምልክት እና አመላካች”** ማለት በመንገድ እና ከመንገድ ውጪ በቋም የሚተከል ምልክት ወይም በመንገዱ ጠርዝ እና/ወይም በተሽከርካሪ መሄጃ መንገዱ ላይ የሚቀባ ቀለም ነው፤

፰. **“የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ”** ማለት አግባብ ባለው ህግ ወይም ፕላን መሰረት ለተሽከርካሪዎች ማቆሚያ እንዲውል በመንገድ ላይ እና ከመንገድ ውጭ የተለየ ስፍራ ነው፤

፱. **“የመኖሪያ ቤት እና አካባቢ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ”** ማለት አግባብ ባለው ህግ ወይም ፕላን መሰረት በመኖሪያ ቤቶች፣ በካምፕ እና በንግድ ቤቶች ላይ ለተሽከርካሪዎች ማቆሚያ እንዲውል የተለየ ስፍራ ነው፤

፲. **“ተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት”** ማለት ተሽከርካሪዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆሙበት ተብሎ በከተማው ውስጥ የተዘጋጀ ወይም የተገነባ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ነው፤

2. **Definition**

In this regulation, unless the context requires otherwise:

1. “**City**” mean the city of Addis Ababa;
2. “City Administration” mean Addis Ababa City Administration;
3. “Bureau” mean the Transport Bureau of Addis Ababa City Administration;
4. "Authority" mean the Authority of Traffic Management of Addis Ababa City Administration;
5. "Traffic controller" shall mean the traffic controller police or the authority's traffic controller, who is authorized by law to enforce the provisions of this regulation and the traffic system to control its implementation and organize the flow of traffic;
6. "Vehicle" shall mean a vehicle that uses a parking area in the City any motorized or no motorized vehicle;
7. "Sign and Indicator" shall mean a sign that is placed vertically on the road and off the road or painted on the edge of the road and/or the carriageway;
8. "Vehicle Parking Area" shall mean an on-road or off-road area set aside for the parking of vehicles in accordance with applicable laws or plans;
9. "Residential and Vehicle Parking Area" shall mean an area set aside for the parking of vehicles on residential, camping and commercial premises in accordance with the applicable law or plan;
10. "Vehicle Parking Service" shall mean the safe keeping of vehicles, a vehicle parking service designed or constructed in the City for the purpose of parking;

፲፩. **"ማኅበራት"** ማለት የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማቶችን ለማስተዳደር ከባለሥልጣኑ ጋር ውል የገቡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማኅበራት ናቸው፤

፲፪. **"የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት"** ማለት የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማቶችን ለማስተዳደር ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ውል በመግባት በግለሰብ ወይም በንግድ ማህበር የመኪና ማቆሚያ ለማስተዳደር የተቋቋመ ድርጅት ነው፤

፲፫. **"ተገልጋይ"** ማለት በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ላይ ተሽከርካሪ በማቆም አገልግሎት ያገኘ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፬. **"መንገድ"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ዋና ዋና መንገዶች፣ መለስተኛ መንገዶች፣ መጋቢ መንገዶች እና የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ናቸው፤

፲፭. **"የመንገድ ዳር ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ በህግ በተፈቀዱ መንገዶች ላይ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ እንዲሆን በምልክትና በቀለም የተለየ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ነው፤

፲፮. **"የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ"** ማለት በህንፃ ህግ መሰረት ተሽከርካሪዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆሙበት በህንፃው ወይም በግቢው ውስጥ ከሕንፃው ጋር በተያያዘ ለሕንፃው ተገልጋዮች የተዘጋጀ ስፍራ ነው፤

፲፯. **"የተሽከርካሪ ማቆሚያ ሕንፃ"** ማለት ለተሽከርካሪዎች ማቆሚያ ብቻ ተብሎ የተገነባና አገልግሎት የሚሰጥ ሕንፃ ነው፤

፲፰. **"ዘመናዊ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ"** ማለት ከዋና መንገድ ውጭ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ታስቦ የተዘጋጀ ቦታ ሆኖ ሜካኒካል ተደራራቢ ፎቅ ያለው ወይም ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ነው፤

፲፱. **"የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት"** ማለት ከመንገድ ውጪ ያለ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ እና አገልግሎት የሚሰጥ ስለመሆኑ የሚሰጥ ሰርተፊኬት ነው፤

11. "Associations" shall mean associations of micro and small enterprises to administer vehicle parking infrastructure that have entered into a contract with the authority;
12. "Private Vehicle Parking Organization" shall mean to administer a parking vehicle infrastructure established by an individual or a business association to manage parking by entering into a contract in accordance with the requirements set by the authority;
13. "User" shall mean anyone who gets a vehicle parking service;
14. "Road" shall mean the main roads, minor roads, feeder roads and internal roads in the City Administration;
15. "Roadside Vehicle Parking Area" shall mean a vehicle parking area with a sign and a marked color for vehicle parking on the legally authorized roads of the City Administration;
16. "Building of Vehicle Parking Area" shall mean vehicles under the building law a place within the building or the premises for the customers of the building to stand safely;
17. "Vehicle Parking Building" shall mean a building built and served only for parking vehicles;
18. "Modern Vehicle Parking Area" shall mean an off-road vehicle parking space designed for vehicle parking services with a mechanical multi-store or technology-based vehicle parking;
19. "Certificate of Competence" shall mean a certificate issued that an off-road vehicle parking service is up to standard and serviceable;

፳ **"የመንግስት መስሪያ ቤት"** ማለት በከፊል ወይም በሙሉ በመንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም ሲሆን የልማት ድርጅትን ይጨመራል፤

፳፩. **"በመንግስት የለሙ ተሽከርካሪ ማቋሚያ ሥፍራዎች"** ማለት ማናቸዉም በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመንግስት በጀት የሚተዳደሩና ከዋናዉ መንገድ ዉጭ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የተገነቡ ወይም የተለዩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ናቸዉ፤

፳፪. **"የፓርኪንግ ግብዓቶች"** ማለት ዉል ለገቡ ማህበራት ወይም ለግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅቶች እንደ ሁኔታዉ በክፍያና ያለክፍያ በባለስልጣኑ የሚቀርቡ የፓርኪንግ ሥርዓት መቆጣጠሪያ ታብሌቶችና ሶፍትዌሮች፣ የትራፊክ ምልክቶች፣ የክፍያ መቀበያ ማሽኖች፣ የፓርኪንግ ደረሰኞች፣ የፓርኪንግ ቦታ ማመላከቻ ቦርዶችና ሌሎች መሰል የፓርኪንግ ሥርዓቱን ለማዘመን ወይም አሰራሩን ለማሻሻል የሚያገለግሉ ግብዓቶች ናቸው፤

፳፫. **"የተሽካርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት ውል"** ማለት ማኀበራት ከባለሥልጣኑ ጋር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎችን ለማስተዳደር የሚገቡት ውል ነው፤

፳፬. **"የአገልግሎት ክፍያ"** ማለት የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የተጠቀመ ማንኛውም ተገልጋይ ላገኘው አገልግሎት የሚፈፅመው ክፍያ ነው፤

፳፭. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. **<u>የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፬. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በከተማው አስተዳደር የሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ፣ በአገልግሎት ሰጪ እና በተገልጋይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፭. **<u>ዓላማ</u>**

በከተማው ውስጥ የሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች በአግባቡ እንዲተዳደሩ በማስቻል የተሳለጠ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋትና ማረጋገጥ ነው፡፡

20. "Government Office" shall mean institution that are partially or fully managed by the government budget and includes a Government Enterprises;
21. "Government Developed Vehicle Parking Areas" shall mean any vehicle parking areas that are partially or fully managed by the government budget and are constructed or designated for vehicle parking outside the main road;
22. "Parking Resources" shall mean parking control system tablets and soft ware's, traffic signals, payment acceptance machines, parking receipts, parking space indication boards and other such things used to update the parking system or improve its operation provided by the authority to the contracting associations or private vehicle parking organizations, as the case may be, with or without payment;
23. "Contract of Vehicle Parking Service Area" shall mean the Contracts for administering car parks by associations with the authority;
24. "Service Fee" shall mean the payment made by any customer who uses the parking space for the service received;
25. "Person" shall mean any physical or juridical person.

**3. <u>Gender Expression</u>**

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine gender.

**4. <u>Scope of Application</u>**

This regulation shall be applicable on the vehicle parking area, service provider and user located in the City Administration.

**5. <u>Objectives</u>**

It is to establish and ensure a streamlined and safe road use system by enabling vehicle parking areas in the City to be properly managed.

## ክፍል ሁለት

## የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ዓይነቶች እና አስተዳደር

**፮. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ዓይነቶች**

፩. የመንገድ ዳር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ፤

፪. ከመንገድ ውጪ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ፤

ሀ) የህንፃ ላይ፣

ለ) የህንፃ ስር፣

ሐ) የመሬት ስር፣

መ) የመሬት ላይ፣ እና

ሠ) ሌሎች ዘመናዊ፤

የተሽከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራዎች፡፡

**፯. የመንገድ ዳር ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ**

፩. የመንገድ ዳር ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ተብሎ በተሰራ መንገድ ላይ ወደ እግረኛ መንገድ ጠርዝ በኩል ያለው እና ልዩ ምልክት የተደረገበት ነው፤

፪. የመንገድ ላይ ምልክትና እና አመላካች ህጎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

ሀ) ባለሥልጣኑ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት የሚከለከልባቸው ስፍራዎችን አግባብ ያለው አካል በሚያወጣው የቀለም ስታንደርድ መሠረት በመንገድ ጠርዝ ላይ ያመላክታል፤

ለ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት በክፍያ በሚፈቀድባቸው ስፍራዎች ባለሥልጣኑ መለያ ቀለሙን በመንገድ ጠርዝ ላይ ያመላክታል፤

ሐ) ባለሥልጣኑ ለዲፕሎማቲክ ተሽከርካሪ ተብሎ ተለይቶ በተያዘ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ሥልጣን ያለው አካል በሚያወጣው የቀለም ስታንደርድ መሠረት የተቀባ የCD ምልክት በመንገዱ ላይ ሊያስቀምጥ ይችላል፤ በዚህም ስፍራ ላይ የሚያገኙት አገልግሎት ከክፍያ ነፃ ይሆናል፤

መ) አካል ጉዳተኛ ለሆኑ አሽከርካሪዎች ብቻ ለተሽከርካሪ ማቆሚያነት የተለዩ ቦታዎች ላይ ባለሥልጣኑ በመንገድ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ላይ በምስል ያመላክታል፤

## PART TWO

## TYPES OF PARKING AREAS AND ADMINISTRATION

**6. Types of Vehicle Parking**

1. Roadside Parking Area;
2. Off Road Parking;
   a) On Building;
   b) Under Building;
   c) Underground;
   d) On the Floor, and
   e) Other Modern Vehicle Parking Areas.

**7. Roadside Vehicle Parking Area**

1. Roadside vehicle parking area located on the side of the sidewalk on a road designed for vehicular movement and specially marked;
2. Subject to road signs and traffic laws:
   a) The Authority shall mark the areas where the service of vehicle parking is prohibited on the edge of the road in accordance with the color standard issued by the relevant body;
   b) The Authority will mark the marking color on the edge of the road in places where parking service is allowed for a fee;
   c) The Authority may place on the road a CD sign painted in accordance with the color standard issued by the competent authority at a vehicle parking area reserved for diplomatic vehicles, the services to get at this location will be free of charge;
   d) The Authority will mark the parking area of the road vehicle in the areas designated for parking of vehicles only for disabled drivers;

ሠ) እቃ ለመጫንና ለማውረድ በተለዩ መንገዶች ላይ ባለሥልጣኑ በመንገድ ጠርዙ ላይ ሥልጣን ያለው አካል በሚያወጣው የቀለም ስታንደርድ መሠረት ያመላክታል፤

ረ) የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በተለየላቸው የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ በነጻ የሚጠቀሙ ይሆናል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) መሠረት ምልክት እና አመላካች የተደረገባቸው አስገዳጅ የመንገድ ላይ ምልክቶች ናቸው፤

፬. ባለሥልጣኑ በመንገድ ላይ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ተብለው በተፈቀዱ ቦታዎች ላይ ማህበራትን አሰማርቶ በክፍያ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**፰. <u>ከመንገድ ውጪ የሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች</u>**

ከመንገድ ውጪ የሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች፡-

፩. ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዙ የመንገድ መስመሮች፣ አቅጣጫ ጠቋሚዎች ፣ የጊዜ ሰሌዳ እና የአገልግሎት ተመኑን የሚገልፅ ማስታወቂያ ሊኖራቸው ይገባል፤

፪. ማንኛውም ከመንገድ ውጪ ለሚገኝ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ተጠቃሚዎች የተለየ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

**፱. <u>ስለ ክፍያ</u>**

፩. ከመንገድ ውጪ የሚገኙ የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት ስፍራ አገልግሎት ክፍያ ተመን ፍትሃዊነትን እና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ አገልግሎቱን በሚያቀርበው አካል የሚወሰን ይሆናል፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የተጋነነ የአግልግሎት ክፍያ ሲኖር ባለሥልጣኑ ከአገልግሎት አቅራቢው ጋር በመነጋገር የአገልግሎት ክፍያ ስታንደርድ ያወጣል፤

e) On designated roads for loading and unloading goods, the Authority indicates on the side of the road according to the color standard issued by the competent body;

f) Free parking for public transport vehicles they may use marked for them.

3. Mandatory road signs marked and indicated in accordance with Sub Article (2) of this Article;

4. The Authority may deploy associations in areas approved for vehicle parking on the road and make them provide services for a fee.

**8. <u>Off Road Parking Areas</u>**

Off Road Parking Areas:

1. They must have routes related to the service, direction indicators, time a board and a notice stating the service rate;

2. For any off-road vehicle parking area, a separate vehicle parking area should be provided for disabled service users.

**9. <u>Payment</u>**

1. The service fee rate of off road private parking companies will be determined by the party providing the service in a manner that takes into account fairness and the existing conditions of the area;

2. Notwithstanding the provision of Sub Article (1) of this Article, when there is an inflated service charge, the Authority will issue a service charge standard in consultation with the service provider;

፫. በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ የሚሰጥ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት ለአካባቢው ነዋሪዎች ከክፍያ ነፃ ይሆናል ፤

፬. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ክፍያን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የአገልግሎት ክፍያ ጥናት አጥንቶ ለከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ ቢሮ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል ፡፡

**፲. ስለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አቅራቢዎች**

የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት አቅራቢዎች ናቸው፡-

፩. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት፤ እና

፪. የመንግስት ተሽከርካሪ ማቆሚያ፤

ናቸው፡፡

**፲፩. ስለግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት አገልግሎት**

የግል የተሽከርካሪ ማቋሚያ ድርጅት ፡-

፩. አገልግሎት መስጠት የሚችለው የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለአገልግሎቱ ብቁ ስለመሆኑ ከባለሥልጣኑ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት ሲችል ነው፤

፪. የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ሙሉ ለሙሉ ለታለመለት ዓላማ ብቻ መዋል አለበት፡፡

**፲፪. የመንግስት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት**

በመንግስት የሚገነባ ከመንገድ ውጪ እና የመንገድ ዳር ተሽከርካሪ ማቆሚያ ሲሆን፡-

፩. ማህበሩ ወይም የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅቱ በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ ጋር የስራ ውል መግባት ይኖርበታል፤

፪. ማህበራቱ ውል ከመግባታቸው በፊት አግባብ ካለው አካል በሥራ መስኩ መስማራት የሚችሉ መሆኑን ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

፫. የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አቅራቢ ከሆነ ውል ከመዋዋሉ በፊት በቅድሚያ በአስተዳደሩ የግዥ ሕግ መሠረት አሸናፊ ሆኖ መቅርብ ይኖርበታል፤

፬. የግል ወይም የማህበራት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አቅራቢ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በወጣው የክፍያ ተመን ይሆናል፤

3. Vehicle parking services provided in residential areas will be free of charge for local residents;
4. Regarding the parking fee, the Authority will study the service fee study and submit it to the Finance Bureau of the City Administration; it will be implemented when allowed.

**10. Vehicle Parking Service Providers**

The vehicle parking service providers are as follows:

1. Private Vehicle Parking Organization; and
2. The Government Vehicle Parking.

**11. Private Vehicle Parking Organization Service**

Private Vehicle Parking Organization:

1. The vehicle parking area that can provide the service is eligible for the service, when he can get a certificate of qualification from the Authority's vehicle parking area;
2. Use of private parking space shall be for its intended purpose only.

**12. Government Vehicle Parking Service**

An off-road and roadside parking lot constructed by the Government:

1. The Association or the Private Vehicle Parking Organization shall first enter into a contract with the Authority;
2. Before entering into a contract, the Associations shall submit a letter of confirmation from the relevant body that they are able to engage in the field of work;
3. If it is a private vehicle parking service provider, it shall first be submitted as a winner according to the Procurement Law of the Administration before entering into a contract;
4. Private or Associations vehicle parking service provider, they can provide vehicle parking services at the rate issued in accordance with Sub Article (4) of Article 9 of this regulation;

፭. በማህበር ወይም በግል የሚተዳደሩ የመንግስት ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ላይ ማኅበሩ ወይም የግል አቅራቢው የመብራት፣ የውሃ፣ የፅዳትና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች የሚሸፍን ይሆናል፤

፮. ለገቢ መሰብሰቢያ የሚሆን ደረሰኝ በፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ባለሥልጣኑ የሚያቀርብ ይሆናል፣

፯. ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የደንብ ልብስ ስታንደርድ መሠረት ማህበራቱ ወይም የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅቶቹ ለፓርኪንግ ሠራተኞቻቸው አንጸባራቂ የደንብ ልብስ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤

፰. ባለሥልጣኑ ለመንግሥት ተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች እና ሌሎች ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን የሚያቀርብ ይሆናል፤

፱. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) ቢኖርም እንደ አስፈላጊነቱ ባለሥልጣኑ የክፍያ መሰብሰቢያ ቴክኖሎጂዎች እና ሌሎች ለስራ አስፈላጊ የሆኑ የግብአት ዓይነቶችን ወስኖ ተዋዋዩ እንዲያቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የተሽከርካሪ ማቆምያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና እድሳት

**፲፫. የተሽከርካሪ ማቆምያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ስለማግኘት**

ማንኛውም በህንጻ ስር እና ህንጻ ዉስጥ የሚገኝ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ለማግኘት የሚከተሉትን መሟላት አለበት፡-

፩. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ደህንነቱ የተጠበቀ ወይም የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፤

፪. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አስፈላጊ የሆኑ ምልክቶች፣ አቅጣጫ ጠቋሚዎች፣ ክፍያ ላላቸው ደረሰኝ፣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያለው አንድ ባለሞያ፣ አስፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል እና የተሟላ የደንብ ልብስ፤

5. In Association or privately administered government vehicle parking areas, the association or the private provider will cover electricity, water, cleaning and other related expenses;

6. Receipts for revenue collection shall be provided by the Authority in accordance with the Financial Administration Law;

7. In accordance with the uniform standards issued by the authority, the Associations or Private Vehicle Parking Organizations shall provide their parking staff with reflective uniforms;

8. The authority will provide technologies used by for government vehicle parking and other resources necessary for work;

9. Notwithstanding Sub Article (6) of this Article, the Authority may, as necessary, determine payment collection technologies and other types of resources necessary for operation and cause the contractor to provide them.

## PART THREE
## CERTIFICATION OF COMPETENCY AND RENEWAL OF VEHICLE PARKING AREA

**13. The Certificate of Competency of the Vehicle Parking Area**

Any underground and in building vehicle parking area must meet the following requirements to obtain a certificate of competency:

1. Whether the vehicle parking area is safe or has a building use permit must first be confirmed from the relevant body;
2. Necessary signs, direction indicators, receipts for payment, one professional with driver's certificate of competency, necessary manpower and complete uniform at the vehicle parking area;

፫. በግንባታ ዲዛይኑ መሠረት ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ሙሉ በሙሉ ለአገልግሎት ለማዋል ዝግጁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**፲፬. የተሽከርካሪ ማቆምያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለ ሚሰጥበት ሁኔታ**

ማንኛውም የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ብቃት ማረጋገጫ የሚጠይቅ ሰው፡-

፩. በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ማመልከቻ ቅፅ መሙላትና መፈረም፤

፪. አመልካች ድርጅቱ ወይም የመንግስት መስሪያ ቤቱ ማመልከቻ ቅፁን በማህተሙ ማረጋገጥ፤

፫. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በተመለከተው መሰረት የሕንፃ ባለቤትነት ወይም የባለይዞታ ምስክር ወረቀት፣ የሕንፃ ውስጠ-ሕንፃዊ ንድፍ ወይም ፕላን፣ የሕንፃው የግንባታ ፈቃድ እና የሕንፃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ኮፒ ማቅረብ፤

፬. በግንባታ ፈቃዱ መሰረት ለሕንፃው ተፈፃሚነት ያለውን የተሽከርካሪ ማቆሚያ ደረጃ መስፈርቶችና ፈቃድ ባለው የሥነ-ሕንፃ ባለሙያ ወይም ድርጅት የተደረገ ልኬት መዘርዘር፤

፭. በክፍያ የሚሠራ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ኮምፒውተራይዝድ የመረጃ ሥርዓት መኖሩን የሚያስገነዝብ ማስረጃን የሚያካትት የተሽከርካሪ ማቆሚያ በቴክኖሎጂ የተደገፈ መገልገያዎች ዝርዝር፤

፮. ለአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ልዩ የተሽከራካሪ ማቆሚያ ስፍራ ማዘጋጀቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**፲፭. የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አገልግሎት ክፍያ እና ዕድሳት**

፩. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ እና የመኖሪያ ቤት እና አካባቢ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እና የእድሳት የአገልግሎት ክፍያ በከተማ አስተዳደሩ የአግልግሎት ክፍያ ደንብ መሠረት ይከፍላል፤

3. It should be ready to use according to the construction design, the vehicle parking area is fully serviceable;

**14. The Issuance of the Vehicle Parking Certificate of Competency**

Any person requesting a vehicle parking certificate of competency:

1. Filling and signing the application form prepared by the Authority;
2. The applicant organization or the government office to confirm the application form with the stamp;
3. According to Sub Articles (1) and (2) of this Article, providing a copy of building ownership or possessor's certificate, building interior design or plan, building construction permit and building use permit;
4. List the vehicle parking level requirements applicable to the building according to the building permit and a measurement made by a licensed architect or firm;
5. A list of technology-enabled facilities for parking, including evidence of the existence of a computerized information system for paid parking;
6. Must ensure that a special vehicle parking area is provided for disabled service users.

**15. Payment and Renewal of Certificate of Competency Service**

1. Vehicle parking area and residence area vehicle parking certificate of competency and renewal service fee shall be paid according to the service fee regulations of the City Administration;

፪. ማንኛውም የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ሰርፊኬት የተሰጠው ሰው ሰርተፊኬቱ የሚያገለግልበት የመጨረሻው ቀን ቀጥሎ ባሉት ሰባት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን መስፈርቶችን በማሟላት ማሳደስ ይኖርበታል፡-

ሀ) የባለሥልጣኑ የእድሳት ማመልከቻ ቅፅ በመሙላት መፈረምና በተሽከርካሪ ማቆሚያ መገልገያው ላይ የተደረጉ ለውጦች ሲኖሩ የተደረጉትን ለውጦች የሚያሳዩ ሰነዶችን ማቅረብ፣

ለ) አመልካች የግል የተሽከርካሪ ቆሚያ ድርጅት ወይም የመንግስት መስሪያ ቤት ሲሆን ማመልከቻ ቅፁን በማህተሙ ማረጋገጥ፡፡

## ክፍል አራት
## ስለተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት

### ፲፮. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ግዴታ

የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባገኘ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ለባለሥልጣኑ ማቅረብና የጊዜ ሰሌዳውን ሲያሻሽል ደግሞ ማሻሻያው ስራ ላይ ከመዋሉ አምስት ቀን በፊት ለባለሥልጣኑ በፅሑፍ ያሳውቃል፤ ባዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል፤

፪. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ስፍራ መግቢያና መውጫ በሮች ላይ ጎልቶ በሚታይ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወይም በተመሳሳይ መገልገያ ላይ ተደርጎ ለተገልጋዮች ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፤

፫. ከባለሥልጣኑ ጋር በመተባበር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለተገልጋዮች ተደራሽ ለማድረግ አግባብ ባላቸው የትራፊክ ምልክቶች ተለይቶ እንዲመላከት ያደርጋል፤

2. Any person who has been issued a vehicle parking service certificate of competency must renew it by meeting the following requirements within seven consecutive working days following the last day of validity of the certificate:

a) Signing the authority's renewal application form and submitting documents showing the changes made to the vehicle parking facilities

b) If the applicant is a private vehicle parking organization or a government office, the application form must be stamped.

## PART FOUR
## SERVICE OF VEHICLE PARKING AREA

### 16. Obligation of the Person Providing Vehicle Parking Service

Any person providing vehicle parking services shall have the following obligations:

1. Within seven working days of receiving the vehicle parking service qualification certificate, prepare a vehicle parking service delivery schedule and submit it to the authority, and when amending the schedule, notify the authority in writing five days before the amendment takes effect; He provides service according to his schedule;
2. Stand out on the entrance and exit doors of the parking service area, make it public to users on a visible notice board or similar device;
3. In cooperation with the Authority, the vehicle parking area is accessible to users to do so, it will be indicated by appropriate traffic signs;

፬. ቀድሞ የመጣ ተገልጋይ ቀድሞ እንዲስተናገድ ያደርጋል፤

፭. በክፍያ ለሚገለገሉ ተገልጋዮች የተያዙና ያልተያዙ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ሥርዓት በመጠቀም አገልግሎት ይሰጣል፤

፮. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተጠባብቀው በሚቆሙ ተሽከርካሪዎች እንዳይጨናነቅ ወይም ከመያዝ አቅሙ በላይ አገልግሎት እንዳይሰጥ ያደርጋል፤

፯. ለተገልጋዮች ሕጋዊ ደረሰኝ በመስጠት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ክፍያ መሰብሰብና ለባለሥልጣኑ ካሳወቀው የክፍያ መጠን በላይ እንዲከፍሉ እንዳይደረግ ይቆጣጠራል፤

፰. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ሠራተኛ ባለሥልጣኑ ባወጣው የደንብ ልብስ ስታንደርድ መሠረት አንጸባራቂ የደንብ ልብስ ለብሶ መገኘት ይኖርበታል፤

፱. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ሠራተኛ ንጽህናውን የመጠበቅ፤ ከአስካሪ መጠጥ፣ ከአደንዛዥ ዕጽ እና መሰል አስነዋሪ ድርጊት የተቆጠበ መሆን አለበት፤

፲. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታውና መገልገያው ፅዳትና ውበት በአግባቡ እንዲያዝና እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

፲፩ በተሽከርካሪ ማቆሚያው የሚገኝ ተሽከርካሪን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ይኖርበታል፤

፲፪.ክትትል በማድረግ በተሽከርካሪ መቆሚያ ቦታው ባልታወቀ ተገልጋይ የተተወ ተሽከርካሪ መኖሩን እንዳወቀ ለፖሊስ ወዲያውኑ በማሳወቅ ተሽከርካሪው ከቆመበት እንዲነሳ፣ እንዲጓጓዝና በፖሊስ ጥበቃ ስር እንዲውል ያደርጋል፤

፲፫.በባለሥልጣኑና በሌሎች ባለድርሻ አካላት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ነክ መረጃ ሲጠየቅ ይሰጣል፤

፲፬.በተገልጋዮች የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች በመቀበል ፍትሐዊነትና አግባብነት ባለው መልኩ ያስተናግዳል፤

4. First come, first served customers;
5. Provides service to paying customers of reserved and unreserved vehicle parking areas using a technology supported information system;
6. Ensures that the vehicle parking service is not overcrowded with parked vehicles or that it does not provide service beyond its carrying capacity;
7. Controls the collection of vehicle parking service fees by providing legal receipts to users and prevents them from paying more than the fee amount notified to the Authority;
8. An employee who is providing service at a vehicle parking area is issued by the Authority according to the uniform standard, he should be present wearing a reflective uniform;
9. To maintain the cleanliness of an employee who is providing service at the vehicle parking area; He must abstain from intoxicating liquor, drugs and similar indecent acts;
10. The vehicle parking area and facilities are kept clean and beautiful;
11. He should be responsible for the safety of the vehicle in the parking lot;
12. As he found out the presence of a vehicle left by an unknown user in the vehicle parking area by monitoring, he immediately informs the police so that the vehicle can be removed from the parking area, transported and used under police protection;
13. Information is provided upon request regarding vehicle parking services by the Authority and other stakeholders.
14. Receives complaints submitted by users and handles them in a fair and appropriate manner;

፲፭. የአሽከርካሪነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለውን ሠራተኛ ጨምሮ ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፡፡

**፲፯. <u>ስለተገልጋይ ግዴታዎች</u>**

የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ተገልጋይ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

፩. በጊዜ ሰሌዳውና በተቀመጡለት ሌሎች መስፈርቶች መሰረት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መጠቀም፤

፪. ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ተብሎ በተወሰነውና ለጊዜው በሚሰጠው ቦታ ብቻ ተሽከርካሪውን ማቆም፤

፫. በክፍያ ለሚያገኘው የተሽከርካሪ ማቆም አገልግሎት የአግልግሎት ክፍያ መፈፀም፤

፬. ከባለሥልጣኑ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ወይም ከትራፊክ ተቆጣጣሪ ጋር የመተባበር፡፡

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>የተከለከሉ ድርጊቶች፣ ስለቅጣትና ቅሬታ አቀራረብ</u>**

**፲፰. <u>የተከለከሉ ድርጊቶች</u>**

፩. የመንግስት የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራን በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

ሀ) ማንኛውም ማህበር ወይም ድርጅት ከባለሥልጣኑ ጋር የአገልግሎት ውል ሳይፈፅም ወይም የፈፀመው ውል ሳይታደስ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መስጠት፣

ለ) ማህበራት ወይም የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት ያለ ደረሰኝ ወይም በሕግ እውቅና ያልተሰጠው ደረሰኝ ወይም የፋይናንስ ቢሮ ካዘጋጀው ደረሰኝ ውጪ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ክፍያ መሰብሰብ፣

ሐ) የማህበር አባልነትን የሚገልፅ ባለሥልጣኑ ከሚያቀርበው የደንብ ልብስ ውጪ ለብሰው የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መስጠት፣

መ) ከባለሥልጣኑ ጋር ውል ከገባው ማህበር አባል ውጪ ለሶስተኛ አካል ማስተላለፍና ቀጥሮ ማሰራት፣

15. Employs other workers necessary for the work, including the worker who has a driver's license, according to the relevant law.

**17. <u>User Obligations</u>**

The Vehicle Parking User has the following obligations:

1. Using the vehicle parking service according to the schedule and other requirements;
2. Parking the vehicle only in the designated and temporary parking area;
3. Making a service charge for the paid parking service;
4. Cooperating with the authorized parking lot supervisor or traffic controller.

**PART FIVE**

**PROHIBITED ACTIONS, PENALITIES AND GRIEVANCE PROCEDURE**

**18. <u>Prohibited Actions</u>**

1. Prohibited Actions in respect of Government Vehicle Parking Areas:
   a) Any association or organization providing vehicle parking services without entering into a service contract with the Authority or renewing the contract;
   b) Associations or private parking organizations collect parking fees without a receipt or a receipt that is not recognized by law or a receipt prepared by the Finance Bureau;
   c) Apart from the uniform provided by the Authority who declares Association membership providing vehicle parking services;
   d) Transferring and hiring to a third party other than the member of the Association who entered into a contract with the Authority;

ሠ) ከባለሥልጣኑ ጋር ውል ገብቶ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የተረከበውን ወይም ያዘጋጀውን ስፍራ እና መሳሪያዎች ከዓላማው ውጪ ለማንኛውም አይነት የንግድ ሥራ ወይም ለሌላ ተግባር ማዋል፣

ረ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ እና መሳሪያዎች ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፣

ሰ) ያለአግባብ ገቢ ለማግኘት ሲባል የክፍያ ማሽን ማበላሸት ወይም የተሳሳተ ክፍያ እንዲወጣ ማድረግ፣

ሸ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ እያለ አገልግሎት መከልከል፣ የአገልግሎት ታሪፍ መደበቅ እና ከታሪፍ በላይ ሂሳብ ማስከፈል፣

ቀ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሰዓት አለማክበር፣ ከአቅም በላይ ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ ማድረግ፣ ተጠቃሚዎችን በቅደም ተከተል ወይም በአግባቡ አለማስተናገድ፤

በ) በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ሠራተኛ ወይም የማህበሩ አባል ንጽህናውን ሳይጠብቅ ወይም አስካሪ መጠጥ ጠጥቶ መገኘት ወይም ጫት መቃም ወይም አደንዛዥ ዕፅ ወስዶ ሥራ ላይ መሠማራት፤

፪. የግል የተሽከርካሪ ማቋሚያ ስፍራ አገልግሎትን በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

ሀ) ማንኛውም የግል የተሽከርካሪ ማቋሚያ ድርጅት ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሳይወስድ ወይም ወቅቱን ጠብቆ ሳያሳድስ አገልግሎት መስጠት፣

ለ) የተሽከርካሪ ማቋሚያ ስፍራን አጠቃቀም ማዛባት ወይም የሕንፃ ማቆሚያ ስፍራን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለሌላ ዓላማ ማዋል፣

ሐ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ሰሌዳ አለማውጣት፣ የወጣውን የጊዜ ሰሌዳ ስራ ላይ አለማዋል፣

e) To use the area and equipment's that have been taken over or prepared for vehicle parking services by entering into a contract with the Authority for any kind of business or other activities other than the intended purpose;

f) Deliberately or negligently causing damage to vehicle parking facilities and equipment;

g) Tampering with a payment machine or causing wrong payments to be made in order to gain illegal income;

h) Denying service while parking, concealing service tariff and overcharging;

i) Not respecting the service hours of the parking lot, allowing vehicles to park beyond capacity, not treating users in order or properly;

j) An employee who is providing service at the parking lot or the association a member does not maintain his cleanliness or is under the influence of intoxicating liquor or chewing chat or taking intoxicating drugs while working;

2. Prohibited Actions in respect of service Private Vehicle Parking Areas:

a) Any private vehicle parking organization without obtaining a certificate of qualification from the authority or renewing it in a timely manner;

b) Distorting the use of a vehicle parking area or using a building's parking area partially or fully for another purpose;

c) Failure to establish a timetable for the provision of vehicle parking services, failure to implement the established timetable;

መ) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለውን ጨምሮ ለተሽከርካሪ ማቆም አገልግሎት አሰጣጥ አግባብነት ያላቸው የቴክኒክ እና የጥበቃ ሠራተኞች በመደበኛነት ሳይመድብ እና የደንብ ልብስ እንዲለብሱ ሳያደርግ አገልግሎት መስጠት፣

ሠ) ተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የክፍያ ተመን ማስታወቂያ ሳይለጥፍ አገልግሎት መስጠት፤

ረ) የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የክፍያ ሥርዓት ግልፅና ወጥነት ያለው እንዲሆን ሳያደርግ አገልግሎት መስጠት፤

ሰ) የባለሥልጣኑ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ተቆጣጣሪ ወደ ተሽከርካሪ ማቋሚያ ቦታ እንዳይገባ ወይም ገብቶ ምልከታ እንዳያደርግ መከልከል ወይም በተቆጣጣሪው የሚጠየቀውን መረጃም ወይም ማስረጃ አለመስጠት፤

ሸ) በክፍያ ለሚሰሩ አገልግሎቶች የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓትን ሥራ ላይ ሳያውል አገልግሎት መስጠት፤

ቀ) በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ሠራተኛ ወይም የማህበሩ አባል ንጽህናውን ሳይጠብቅ ወይም አስካሪ መጠጥ ጠጥቶ መገኘት ወይም ጫት መቃም ወይም አደንዛዥ ዕጽ ወስዶ ሥራ ላይ መሠማራት፤

፫. ተገልጋይን በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

ሀ) የተሽከርካሪ ሰሌዳ ሳይለጥፍ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መጠየቅ፣

ለ) ባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ለዲፕሎማቲክ ወይም ለአካል ጉዳተኞች በለያቸው የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ላይ መጠቀም፣

ሐ) ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ያለመፈጸም፡፡

d) providing services without regularly assigning relevant technical and security personnel for the provision of vehicle parking services, including those with a driver's license, and without making them wear uniforms;

e) Vehicle parking service without posting fee rate notice providing services;

f) Providing services without making the payment system of the building parking service transparent and consistent;

g) Preventing the Authority's vehicle parking inspector from entering the vehicle marking area or from entering and observing or not providing the information or evidence requested by the inspector;

h) To provide parking facilities for paid services without using modern information technology systems;

i) An employee who is providing service at a vehicle parking area or a member of the association does not maintain cleanliness or is present under the influence of intoxicating liquor or chewing chat or taking intoxicating drugs while working.

3. Prohibited Actions in respect of Users:

a) Requesting a vehicle parking service without posting a vehicle plate;

b) Use of vehicle parking areas designated by the Authority as specially designated for Diplomatic or disabled persons;

c) Failure to pay the appropriate service charge for vehicle parking services.

## ፲፱.ስለ አስተዳደራዊ እርምጃ

፩. በወንጀል ሕግ እና በሌላ አግባብ ባለው ሕግ የሚኖረው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ደንብ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡-

ሀ) ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ፈጽሞ ከተገኘ ድርጊቱን እንዲያቆም ወይም እንዲያርም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

ለ) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ደርጊቱን መፈጸም ያላቆመ ወይም የእርምት እርምጃ የማይወስድ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ እንደ አግባብነቱ ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ የተመለከተው አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፤

ሐ) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ወይም አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ባለመታረም የጥፋት ድርጊቱን መፈጸም የማያቆም ወይም የእርምት እርምጃ የማይወስድ የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት ወይም ማህበር ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይታገዳል፤

መ) የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱን ማገድ በቂ ሆኖ በማይገኝበት ጊዜ ወይም እግዱ በተሰጠ በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጥፋት ድርጊቱን በማቆም ወይም የእርምት እርምጃ በመውሰድ እግዱ እንዲነሳለት ካልጠየቀ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ይሰረዛል፤

ሠ) ጥፋት የፈጸመው ከባለሥልጣኑ ጋር ውል የተዋዋለ ማህበር ወይም የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ወይም አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ባለመታረም የጥፋት ድርጊቱን ካላቆመ ወይም የእርምት እርምጃ ካልወሰደ ውሉ ይሰረዛል፡፡

፪. በዚህ ደንብ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ እና ለአካል ጉዳተኞች ወይም በልዩ ሁኔታ በለያቸው የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ላይ የሚገለገል ተገልጋይ አግባብ ባለው የትራፊክ ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 19. Administrative Measures

1. Subject to the provisions of criminal law and other relevant laws any person who violates this regulation will be subject to the following Administrative Measures:

   a) Any person who is found to have committed the offenses listed in Article 18 of this regulation for the first time, to stop or correct his actions will be given a written warning;

   b) When it is found that the Authority does not stop performing the act according to the warning or does not take corrective action, the Authority shall be punished with an administrative fine as indicated in the table attached to this regulation;

   c) Failure to correct the warning or administrative fine, if it is a private vehicle parking organization or association that does not stop committing the offense or does not take corrective action, the certificate of qualification will be suspended;

   d) When the suspension of the qualification certificate is not sufficient or if, within 30 consecutive days of the suspension, he does not request the suspension to be lifted by ceasing the offense or taking corrective action, his certificate of competency will be revoked;

   e) If the offending association or private vehicle parking organization that has contracted with the Authority does not stop the offending act or take corrective action due to a warning or an administrative fine, the contract will be cancelled.

2. Who refuses to pay the service fee according to this regulation or the Authority shall be liable in accordance with the relevant traffic laws for the diplomatic community and the disabled or disabled persons or the customers who use the specially designated parking areas.

፫. ባለሥልጣኑ የክትትል ባለሙያዎች ጥፋት ፈጻሚዎችን በመለየትና አግባነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማያያዝ ለባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያቀርባሉ፤

፬. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ ላይ የተከለከለ ተግባር ለፈጸመው ማህበር ወይም የግል ድርጅት የቀረበበትን ክስ በጽሁፍ በማሳወቅ መልስ ይዞ እንዲቀርብ ጥሪ ያደርጋል፤

፭. ጥሪ የደረሰው ማህበር ወይም የግል ድርጅት ጥሪው በደረሰው አምስት ቀናት ውስጥ መልሱን በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፤ ባለሥልጣኑ ጉዳዩን መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፳. <u>ስለቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት</u>

፩. ማናቸውም ቅሬታና አቤቱታ አቅራቢ በመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎቱን ለሰጠው የሥራ ክፍል በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤ ቅሬታው የቀረበበት የስራ ክፍል ለቀረበው ለአቤቱታ በ፭ (አምስት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ምላሽ መስጠት አለበት፤

፪. ቅሬታው የቀረበበት የሥራ ክፍል በሰጠው ምላሽ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በክፍለ ከተማ ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ በማዕከል ለባለሥልጣኑዋና ዳይሬክተር ይሆናል፤

፫. በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን በ፭ (አምስት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሊያቀርብ ይችላል፤

፬. አቤቱታ የቀረበለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቤቱታው በቀረበለት በ፭ (በአምስት) የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ውሳኔ ይሰጣል፤ የባለሥልጣኑ ዳይሬክተር ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

3. The authority's monitoring experts identify the perpetrators of the offense and attach relevant evidence and submit to the authority for administrative action to be taken;
4. The Authority shall inform the association or private organization that has committed an act prohibited by this regulation in writing and call for an answer;
5. The association or private organization that received the call shall submit the answer in writing to the authority within five days of receiving the call, the authority will investigate the matter and take the necessary decision.

**20. <u>Grievance Procedure</u>**

1. Any grievance and petitioner can submit the complaint within seven consecutive working days to the department that provided the service in the first instance, the working department to which the complaint was submitted must give a written response to the complainant within 5 (five) consecutive working days;
2. A complainant who is dissatisfied with the response of the work department, to which the complaint was submitted, submits the complaint to the general manager of the branch office in the sub-city within seven consecutive working days; He will be the Director-General for the Authority at the Centre;
3. Complaint of dissatisfaction with the decision given by the general manager of the branch office a petitioner may submit the complaint in writing to the Executive Director of the authority within 5 (five) consecutive working days;
4. The Executive Director of the Authority to whom a petition is submitted shall issue a written decision within 5 (five) working days of the petition being submitted, the decision of the Authority Director shall be final.

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፩. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፪. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ካቢኔው ያወጣው ደንብ እና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፫. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ለማውጣት ይችላል፡፡

**፳፬. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከ መጋቢት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፮ ቀን/፪ሺ፲፮ ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ ደሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## PART SIX

## MISCELLNEOUS PROVISIONS

**21. Duty to Cooperate**

Any person shall be obliged to respect and enforce this regulation.

**22. Inapplicable Laws**

Any regulations, directives and customary practices of the City Administration that are contrary to this regulation shall not apply to the matters covered by this regulation.

**23. Power to Issue Directives**

The Authority may issue directives to enforce this regulation.

**24. Effective Date**

This regulation shall enter into force as of this 04th day of April, 2024.

**Addis Ababa 04th Day of April, 2024.**

**Adanech Abebe Desa**

**Mayor of Addis Ababa City**

## አባሪ፡- የአስተዳደራዊ ቅጣት ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | አስተዳደራዊ የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ግልጋሎት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያሳድሱ አገልግሎት መስጠት፤ | አንድ መቶ ሺህ ብር ብር(፻ ሺ.ብር) |
| ፪ | የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቋሚያ አገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ሰሌዳ አለማውጣት ወይም የወጣውን ስራ ላይ አለማዋል፤ | አንድ መቶ ሺህ ብር ብር(፻ ሺ.ብር) |
| ፫ | በክፍያ ለሚሰሩ አገልግሎቶች መንጃ ፈቃድ ያለውን ጨምሮ ለሕንፃው ተሽከርካሪ ማቆምያ አገልግሎት አሰጣጥ የቴክኒክ እና የፀጥታ ሰራተኞች በመደበኛነት አለመመደብ | ሶስት ሺ. ብር (፫ሺ.ብር) |
| ፬ | በክፍያ ለሚሰሩ አገልግሎቶች የሕንፃ ማቆሚያ አገልግሎት የቴክኒክ ወይም የፀጥታ ሠራተኛ የደንብ ልብስ እንዲለብስ አለማድረግ፤ | ሶስት ሺ. ብር (፫ሺ.ብር)) |
| ፭ | የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት ወይም ማህበራት የቴክኒክ ወይም የጥበቃ ሠራተኛ አንጸባራቂ የደንብ ልብስ ያልለበሰ፤ | አንድ ሺ. አምስት መቶ ብር (፩ሺ.፭፻ብር) |
| ፮ | ግልፅና ወጥነት ያለው የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የክፍያ ስርዓት እንዲኖር ወይም እንዲዘረጋ አለማድረግ፤ | አስር ሺ. ብር ((፩ሺ.፭፻ብር) |
| ፯ | በክፍያ ለሚሰሩ አገልግሎቶች የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን በቴክኖሎጂ የመረጃ ስርዓትን ስራ ላይ አለማዋል፤ | አስር ሺ. ብር (፲ ሺ.ብር) |
| ፰ | ምስክር ወረቀት ሳያወጡ የሕንፃ የተሸየብቃት ማረጋገጫ ከርካሪ ማቆም አገልግሎት መስጠት፤ | አሥር ሺህ ብር (፲ ሺ.ብር) |
| ፱ | የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቋሚያ አገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ሰሌዳ አለማውጣት ወይም የወጣውን ስራ ላይ አለማዋል፤ | መቶ ሺ. ብር (፻ ሺ.ብር) |

## Appendix: Administrative Penalty Table

| No | Types of Fault | Administrative Penalty Amount |
|---|---|---|
| 1 | Providing building vehicle parking service without renewing certificate of competency credentials | One Hundred Thousand Birr (100,000.00) |
| 2 | Distortion of the use of the vehicle parking area of the building or the partial or complete use of the parking area of the building for another purpose | One Hundred Thousand Birr (100,000.00) |
| 3 | Failure to establish a schedule for the provision of building vehicle parking services or failure to implement one | Three Thousand Birr (3,000.00) |
| 4 | Non-regular allocation of technical and security personnel for the building's vehicle parking services, including those with driver's licenses for paid services | Three Thousand Birr (3,000.00) |
| 5 | Failure to have technical or security staff wear uniforms for building vehicle parking services for paid services | One Thousand Five Hundred Birr (1,500.00) |
| 6 | Private vehicle parking organization or technical associations or a security guard not wearing a reflective uniform | One Thousand Five Hundred Birr (1,500.00) |
| 7 | Failure to establish or implement a clear and consistent payment system for building vehicle parking services | Ten Thousand Birr (10,000.00) |
| 8 | Failure to building vehicle parking for paid services use of technology information systems in places | Ten Thousand Birr (10,000.00) |
| 9 | Building vehicles without issuing a certificate of competency stop providing services | One Hundred Thousand Birr (100,000.00) |